የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲን ዓላማና
ተግባራት ለማስተዋወቅ የተዘጋጀ

# ግባችን ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ ትክክለኛ መረጃ ማመንጨትና ማሰራጨት ነው!

በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ /Central Statistical Agency
በሕዝብ ግንኙነትና መረጃ ሥርጭት ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ
☎ 01 11 55 30 11/01 11 57 81 56/01 11 56 38 82/01 11 11 44 45
✉ 1143 ፋክስ: 011-1550334
ድረ ገጽ: www.csa.gov.et አዲስ አበባ/ኢትዮጵያ

መጋቢት 2004 ዓ.ም.

# ማ ው ጫ


| ርዕስ | ገፅ |
| --- | --- |
| • መግቢያ ........................................ | 2 |
| • የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ተልዕኮ፣ ራዕይና ዕሴቶች ...... | 5 |
| • ኤጀንሲው የተቋቋመበት ዓላማ .............................. | 6 |
| • የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር .............................. | 7 |
| • ለኤጀንሲው ራዕይና ተልዕኮ ስኬት እየተከናወኑ ያሉ ዋና ዋና ተግባራት ........................................ | 9 |
| • አገሪቱ የምትገኝበት የለውጥና የልማት ሂደትና መረጃ ስላለው ጠቀሜታ .................................... | 11 |
| • የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓላማዎች.............................. | 12 |
| • የዕቅዱ መሰረታዊ አቅጣጫዎች (Strategic Pillars) ............... | 12 |
| • በ25ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች መሠረታዊ የኮሙኒኬሽንና የማስተዋወቂያ ስልቶች መነሻ .................................... | 16 |

## መግቢያ

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የአገሪቱን የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የሥነ-ሕዝብ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በመተንተንና በማቀናበር ለመረጃ ተጠቃሚ የሚያቀርብ የመንግሥት አካል ነው፡፡

ኤጀንሲው ይህን ተልዕኮውን ለመወጣት ሰኔ 18/1952 ዓ.ም. ሲመሠረት ከነበረው ከ20 ከማይበልጡ ሠራተኞችና ኋላቀር ከሆነ ደረጃ በመነሳት የተጀመው ሥራ በአሁኑ ወቅት ከ1700 በላይ ቋሚ ሠራተኞችና በየዓመቱ ከ2000 ያላነሱ ኮንትራት ሠራተኞችን በማሠማራትና ከፍተኛ የሎጂስቲክ አቅም ፈጥሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተቋሙ በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ትግበራም በአጭር ጊዜ ቢያንስ ለአፍሪቃ የስታቲስቲክስ መ/ቤቶች ሞዴል በሚሆንበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡

መ/ቤቱ ይህን ግዙፍ አገራዊ ተግባር ለማከናወን ከሌሎች የፌዴራል መ/ቤቶች በሰፋ ሁኔታ መዋቅሩን በ25 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በማደራጀት እያሉ ባለሙያዎችንና ሠራተኞችን በማሠማራት የመረጃ መሰብሰቡን ተግባር እያከናወነ ይገኛል፣ ይህ በየቤቱ፣ በእያንዳንዱ የአርሶ አደር ማሳ፣ በየአርብቶ አደሩም ሆነ በየማምረቻ ድርጅቶች ... ወ.ዘ.ተ በመንቀሳቀስ የሚደረገው የመረጃ መሰብሰብ ሥራ በብዙ ድካምና ውጣ ውረድ ከተከናወነ በኋላ በቅ/ጽ/ቤቶች የሚደረገው የማደራጀት ሥራ ተሠርቶ ወደ ዋናው መ/ቤት ይላካል፡፡ በቆጠራም ሆነ በናሙና ጥናት የሚሰበሰበው ይህ ጠቃሚ መረጃ በሳይንሳዊ መንገድ ተገቢው ትንተናና የማቀናበር ሥራ ከተከናወነ በኋላ በሕትመትና በሲዲ /CD/ እንዲዘጋጅ ተደርጎ ለተጠቃሚ ይሠራጫል፡፡

በዚህ መልክ በሪፖርት ሲገለጽ ቀላል የሚመስለው እያንዳንዱ የቆጠራም ሆነ የናሙና ጥናት ስታቲስቲካዊ መረጃ ወደ መረጃ ተጠቃሚዎች ከመድረሱ አስቀድሞ ግዙፍ የካፒታል በጀት፣ ሎጂስቲክስና ከፍተኛ የሰው ቁጥር

የዋለበት የአገሪቱ ትልቅ መዋዕለንዋይና ጥረት ይፈስበታል። ይህ በብዙ ድካምና ልፋት የሚቀናበረው መረጃ መልሶ አገሪቱ ለጀመረቻቸው የልማት እቅዶች፣ የቴክኖሎጂ ምርምሮችና አዳዲስ ግኝቶች በአግባቡ መከናወንና ለክትትልም ያገለግላሉ። የትምህርትና የጤና ፖሊሲዎችን ለመቅረጽና በሥራ ላይ የዋሉ የእድገት እርምጃዎችን አተገባበር ለመከታተልና ለመገምገም ጠቋሚና እጅግ ጠቃሚ ግብአቶች ናቸው።

እነዚህን ጠቃሚ መረጃዎች ሰብስቦና አቀናብሮ ለተጠቃሚው ለማሠራጨት በሚደረገው አገራዊ ጥረ ውስጥ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው። ከሁሉም በላይ የመረጃው ምንጭ የሆነው ሕብረተሰብ ይህን ከፍተኛ ኃላፊነት በማስተግበር ሒደት ውስጥ የአንበሳውን ድርሻ መወጣት ይኖርበታል። ስታቲስቲካዊ መረጃዎች የሚሰበሰቡት አገሪቱ ለዘረጋቻቸው የእድገትና የልማት ዕቅዶች ተግባራዊነት ተገቢውን የመነሻ ግብአት ለመስጠት ነው፣ ያለነዚህ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ድጋፍ በውጤት የሚቋጭ ልማት የለም። ይህን እውነት መላው የአገራችን ሕዝብ በሚገባ ሊገዘነበው ይገባል።

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ያሠማራቸው መረጃ ሰብሳቢዎች በእያንዳንዱ ዜጋ መኖሪያም ሆነ የሥራና የማምረቻ ቦታ እየተገኙ መረጃ የሚጠይቁት ይህንን አገራዊ የመረጃ ፍላጎት ለማሟላት ብቻ ነው። በመ/ቤቱ ዘንድ የእያንዳንዱ ዜጋ የግል ሁኔታ በጥንቃቄ በኮድና በምስጢር የሚያዝ ነው። የሚሰጡ መረጃዎች ሁሉ በሳይንሳዊ ዘዴ በጋራ ተተንትነውና ተቀነባብረው በጠቅላላ ውጤት የአገር ሀብትና መገለጫ ሆነው ከመውጣታቸው በስተቀር ስለአንድ ግለሰብ ማንነት የሚገልፁት አንዳች ምክንያት የለም። ይህን መላው የአገራችን ሕዝብና ዜጎች በሚገባ ሊያጤኑት ይገባል። መ/ቤቱ እስካሁን መረጃ ለመሰብሰብ በመስክ በተገኘበት ጊዜ ሁሉ መላው ሕዝብና ዜጎች ያልተቋረጠ ድጋፍና ትብብር ሊያደርጉለት ቆይተዋል። በጥናቶች ውስጥ እጅግ በርካታ ቤተሰቦች፣ የማምረቻና የማከፋፈያ ድርጅቶች፣ አገልግሎት ሰጭና ተቀባይ የሆኑ ተቋማት ሁሉ በናሙናነት ተመርጠው ስለቸኙ፣ ታከተኝ ሳይሉ የተጠየቁትን ሁሉ ትክክለኛ መልስ በመስጠት የዜግነት መብታቸውንና ግዴታቸውን ያለምንም ማቅማማት ሲወጡ ቆይተዋል። ይህ ወደፊትም ተጠናክሮ መቀጠል አለበት።

ይሁን እንጅ አንዳንድ ዜጎች የመረጃ መሰብሰቡን ዓላማ በውል ባለማጤንና ያለውን አገራዊ ፋይዳና የጋራ ጥቅም ባለመረዳት አልፎ አልፎ ለመረጃ ሰጭዎቻችን ትክክለኛ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ታይተዋል። ይህ በፍፁም ከአንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ የማይጠበቅና በሕግም የሚያስጠይቅ አፍራሽ ተግባር ነው። እያንዳንዱ ዜጋ መረጃ የመጠየቅና የመጠቀም እንዲሁም መረጃው ለምን ዓላማ እንደሚውል ጥያቄ የማቅረብ መብት እንዳለው ሁሉ በሌላ በኩል ለአገርና ለወገን የጋራ ጥቅም ሲባል ለሚሰበሰቡ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች እንዲተባበር ሲጠየቅ ትክክለኛ መረጃ የመስጠት ሕገ መንግሥታዊ ግዴታም አለበት። ይህ በትክክል ትኩረት ሊያገኝ የሚገባ አገራዊ ጉዳይ ነው። የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የተቋቋመበት ዋነኛ ዓላማ የአገሪቱን የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የሥነ-ሕዝብ መረጃዎች በቆጠራ፣ በናሙና ጥናትና ከአስተዳደር መዛግብት በመሰብሰብ፣ በመተንተንና በማቀናበር ለመረጃ ሰጭው ሕብረተሰብ ማሠራጨት ነው። ይህ መረጃዎችን የማሠራጨት አጠቃላይ ሒደት የሚከናወነው ደግሞ በመላው ሕዝብ የቅርብ ድጋፍና ያልተቋረጠ ትብብር ብቻ ነው። በዚህ ረገድ መ/ቤቱ ዛሬም ይህ የተለመደ ድጋፍና ትብብር እንዳይለየው የአደራ ጥሪውን በድጋሚ ያስተላልፋል።

የዚህ ቡሮሹር መሰናዳት ሁነኛ ሀሳብ የመነጨውም ይህን ያልተቋረጠ ትብብር ለማስቀጠል ነው። በሌላም በኩል በ25ቱም ቅ/ጽ/ቤቶቻችን አማካኝነት በየትኛ ውም ሥፍራ ለሚሠማሩት መረጃ ሰብሳቢዎች ሥራ መቃናት እንዲያግዝ ሆኖ የተዘጋጀ ነው። በመላ አገሪቱ የሚሠማሩት መረጃ ሰብሳቢዎች በየደረሱበት ሁሉ የመ/ቤቱን ዓላማ፣ ራዕይና ተልዕኮ በሚመቻቸው መንገድ ለማስተማርና ሕብረተሰቡን ለማስገንዘብ እንደመነሻ እንዲሆናቸውም ጭምር ነው።

በመሆኑም እያንዳንዱ የመ/ቤቱ አካል ባለሙያና ሠራተኛ ከሕብረተሰቡ ጋር የመገናኘት አጋጣሚ ባገኘ ቁጥር በመልካም ሥነምግባርና ፍፁም በሆነ ኢትዮጵያዊ ጨዋነት በመታነጽ ሕብረተሰቡን የማሳወቅና የማስገንዘብ ኃላፊነት ተጥሎበታል። በተለይም መረጃ ሰብሳቢዎች ከሕብረተሰቡና ከእያንዳንዱ መረጃ ሰጭ ጋር በቀጥታ የመገናኘት ዕድሉ ያላቸው የመ/ቤታቸውን ራዕይና ተልዕኮ በቀላል የመግባቢያ ቋንቋ በማስገንዘብ ዋነኛ

ተልዕኳቸው የሆነውን ትክክለኛ መረጃ የመሰብሰብ አደራ መወጣት ይኖርባቸዋል። የሚሰበሰበው መረጃ ለአገርና ለወገን የጋራ ጥቅም መሆኑንና ሕብረተሰቡ ለዚህ ተግባር የመተባበር ኃላፊነትና ግዴታም እንዳለበት ማስተማር ይጠበቅባቸዋል። በየደረሱበት ሥፍራ ሁሉ ራሱን ሕዝቡን በመምሰል የሚበላውን በልተው፣ ወግና ባህሉን አክብረውና ተግባብተው እስከቀረቡ ድረስ ትክክለኛ መረጃ ሊያገኙ እንደሚችሉ ይታመናል።

ለዚህ ቡሮሹር መዘጋጀት እንደዋነኛ ምክንያት የሆነው ትክክለኛ መረጃ ለመሰብሰብና በወቅቱ በመተንተንና በማቀነባበር ለመረጃ ተጠቃሚው በማሠራጨት የተሻለ ተደራሽ ለመሆን ስለሆነ ይህ ጥረት የመረጃ ሰብሳቢዎቻችንና ባጠቃላይም የመ/ቤታችንን ተልዕኮ ለማስፈፀም ያግዛል የሚል ጽኑ እምነት አለ። የቡሮሹሩ ቀጣይነት በሁሉም የመ/ቤቱ ሠራተኞች ተሳትፎ የሚዳብር ነው።

## የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ተልዕኮ፣ ራዕይና ዕሴቶች

### ተልዕኮ

ለልማት ፖሊሲዎች ቀረፃ፣ ለዕቅድ ዝግጅት፣ ለጥናትና ምርምር፣ እንዲሁም ለክትትልና ግምገማ ግብዓት የሚሆን ወቅታዊ፣ የጥራት ደረጃውን የጠበቀና የተቀናጀ የኦፊሽያል ስታቲስቲክስ መረጃ ማመንጨት፣ ማሠራጨትና የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተሙን ማስተባበር፣

### ራዕይ

በ2012 ዓ.ም. በስታቲስቲክስ መረጃ ጥራትና አቅርቦት በአፍሪቃ በሞዴልነት የሚጠቀስ መሪ ተቋም መሆን፣

ዕሴቶች

- ወቅታዊና ጥራት ያለው የስታቲስቲክስ መረጃ እናቀርባለን፣
- የተቀናጀና ዘመናዊ አሰራር እናሰፍናለን፣
- ለሰው ሀብት ልማት ትኩረት እንሰጣለን፣
- የቡድን ስራ እናሰፍናለን፣
- የተገልጋዮችን ፍላጎት ያገናዘበ ስታቲስቲካዊ ጥናቶች እናከናውናለን፣
- ለሙያ ክብርና ፍቅር መስጠት፣
- ለመረጃ ሰጭዎቻችን ተገቢውን አክብሮት መስጠት፣
- ግልፅነት ፣ ተጠያቂነትና አሳታፊነት መርሆችን ነው፣
- ህግና ደንብ በአግባቡ በመተግበር ለውጤት እንተጋለን፣
- ባስቸጋሪ ሁኔታ ዉስጥ ስራ ተባብረን እንሰራለን፣
- ከልማት አጋሮች ጋር መልካም ግንኙነት እንፈጥራለን፣
- የመማርና የመለወጥ ተነሳሽነትን መኖር፣
- ለዓለም አቀፍ ዕውቅናና ተወዳዳሪነት ትኩረት እንሰጣለን፣
- ጥሩ የሥራ ግንኙነት ለውጤታችን የጐላ ሚና እንደሚኖረው እናምናለን፣

## ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፵፪/፲፱፻፺፯ (442/1997) የሕጋዊ ሰውነት መብት የተሰጠው የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት ነው።

### ኤጀንሲው የተቋቋመበት ዓላማ

1. በቆጠራ፣ በናሙና ጥናት፣ በማያቋርጥ ምዝገባና ከአስተዳደር መዛግብት የተሰበሰቡ የኢኮኖሚያዊ፣ የማህበራዊና የሥነ ሕዝብ፣ የስታቲስቲክስ መረጃዎችን በተቀናጀ አሠራር ሰብስቦ፣ አቀነባብሮና ተንትኖ ለተጠቃሚዎች የማሠራጨት፣

2. የመንግሥት መ/ቤቶችና ሌሎች አካላት የስታቲስቲክስ መዝገብ አያያዝ፣ የማያቋርጥ የምዝገባ አሠራርና የሪፖርት ሥርዓት እንዲዘረጉ የቴክኒክ ምክርና ድጋፍ የማድረግ፣ እንዲሁም ስለማያቋርጥ ምዝገባ፣ የአስተዳደራዊ መዛግብት መረጃ ክምችቶች በመፍጠርና የአያያዝ ሥርዓት ለማደራጀት ምክርና ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል አቅም የመገንባት ይሆናል።

## የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

ኤጀንሲው የአገሪቱ የስታቲስቲክስ ማዕከል ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፣

1. የስታቲስቲክስ መረጃዎችን በቆጠራ፣ በናሙና ጥናቶች፣ በማያቋርጥ ምዝገባና ከአስተዳደር መዛግብት ይሰበስባል፣ እንዲሰበሰቡም ያደርጋል፣ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ያደራጃል፣ ያቀነባብራል፣ ይተነትናል፣ በጽሑፍ ያወጣል፣ ያሰራጫል፣

2. በየወቅቱ የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የስታቲስቲክስ ፕ ሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ የበጀት ረቂቅ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣ ሌሎች የመንግሥት መ/ቤቶችና ተቋማትም በሥራ ላይ ማዋላቸውን ያረጋግጣል፣

3. ከመንግሥታዊ መ/ቤቶች ወይም ተቋማት ወይም የግል ድርጅቶች በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት የስታቲስቲክስን ሥራ በተመለከተ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣

4. የስታቲስቲክስ አሠራር ዘዴዎችን በተመለከተ የጥናትና ምርምር ተግባር ያከናውናል፣ የተገኙ ውጤቶችንም በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣

5. በመንግሥት መ/ቤቶችና ተቋማት፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና በግሉ ዘርፍ ውስጥ በስታቲስቲክስ ሥራ ለተሰማሩ ሠራተኞች መሠረታዊ አጫጭር የስታቲስቲክስ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ይሰጣል፣

6. አገራዊ የስታቲስቲክስ ሥራን ለማሻሻልና የሥራ መደራረብን ለማስወገድ የሥራ አፈጻጸም ኘሮግራሞችና መመሪያዎችን ያወጣል፣ በሥራ ላይ መዋላቸውንም ያረጋግጣል፣

7. የሚሰበሰቡትን መረጃዎች በተመለከተ ሥርዓት ይወስናል፣ ትርጉምና ምደባ ያወጣል፣ የሚሰበሰበውን መረጃ ዓይነትና ዝርዝር እንደዚሁም የሚሰበሰቡበትን ጊዜ ይወስናል፣ በዚሁ መሠረት እንዲፈፀም ያደርጋል፣

8. ዓለም አቀፍ ስታቲስቲካዊ ደረጃን ለመጠበቅ በአገሪቱ የሚሰበሰቡ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ከሌሎች አገሮች፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጋር ተነጻጻሪ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

9. በሀገራዊ የቆጠራና ናሙና ጥናት አማካይነት የሚሰበሰቡ ኢኮኖሚያዊ፣ የማህበራዊና የዲሞግራፊያዊ መረጃዎች የክልል መንግሥታትን ፍላጎት የሚያሟሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

10. የክልል መንግሥታት ጥያቄ ሲያቀርቡ አስፈላጊውን የስታቲስቲክስ መረጃ የመሰብሰብ፣ የማደራጀት፣ የመተንተንና በጽሑፍ የማውጣትና የማሠራጨት ዝግጅትን በመምራትና በማስተባበር ረገድ ይረዳል፣ እንደዚሁም የስታቲስቲክስ መዝገብ አያያዝ ሥርዓት መቋቋሙን ያረጋግጣል፣

11. የስታቲስቲክስ ተግባራትን ለማከናወን ከለጋሽ አገሮችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የገንዘብ፣ የማቴሪያልና የቴክኒክ ዕርዳታ የሚገኝበትን ሁኔታ በማመቻቸት በሚኒስትሩ እንዲፀድቅለት ያቀርባል፣

12. ከተያዘው ዕቅድና ፕሮግራም ውጪ ለሚቀርቡ የጥናት ጥያቄዎች ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ከመንግሥት መ/ቤቶችና ተቋማት እንዲሁም ከሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ለጥናቶቹ የሚያስፈልጉ የተወሰኑ ወጪዎችን እንዲሸፍኑ በማድረግና ቅደም ተከተል በማውጣት ጥናቶችን ያከናውናል፣

13. በሁሉም የስታቲስቲክስ ዘርፎች በስታቲስቲክስ ሙያ ሥልጠና ለሚሰጡ ማዕከላት ከውጪ ስለሚገኝ የሥልጠናና የቴክኒክ ዕርዳታ አጠቃቀም አስፈላጊውን ምክር ይሰጣል፣

14. የስታቲስቲክስ መዝገብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብን በሚመለከት የመንግሥት መ/ቤቶች ወይም ተቋማትና ሌሎች አካላት በተግባር

ሊያሟሉትና ሊከተሉት የሚገባውን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፣

15. በስታቲስቲክስና ተመሳሳይ ዘርፍ ከተቋቋሙ አገራዊ የሙያ ማህበራት ጋር ትብብር ይፈጥራል፣ እንደአስፈላጊነቱ ኮንፈረንሶች በሚካሄዱበት ጊዜ አስፈላጊውን ዕርዳታ ይሰጣል፣

16. ለሚያሰራጫቸው የጥናትና የቆጠራ ውጤቶች እንዲሁም ጥሬ መረጃዎች ለመጠቀም የአገልግሎት ክፍያ ሊጠይቅ ይችላል፣

17. በስታቲስቲክስ ጉዳይ ሁሉ ለመንግሥት ምክር ይሰጣል፣

18. በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎችና አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፣ ስታቲስቲክስን የሚመለከቱ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።

## ለኤጀንሲው ራዕይና ተልዕኮ ስኬት እየተከናወኑ ያሉ ዋና ዋና ተግባራት

የአንድን አገር የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የሥነሕዝብ ሁኔታን የሚያንፀባርቁ አጠቃላይ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ድህነትን ለመቅረፍ የሚቀረጹ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ለማዘጋጀትና በተግባር ላይ ሲውሉም ያስገኙትን ውጤት ለመገምገም፣ ለመከታተልና የተለያዩ ጥናቶችን ለማካሄድ አስፈላጊና መሠረታዊ ግብዓት መሆናቸው ይታወቃል። መንግሥት የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓቱን በመደገፍ አገራዊ ልማቱንና የመልካም አስተዳደር ውጤቶችን ለመለካት፣ ለክትትልና ግምገማ ሥርዓቱ ከፍተኛ ድጋፍ የሚሰጡትን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን የሚዳስሱ ጥናቶችና ቆጠራዎችን ለማካሄድ የሚረዳ በአንፃራዊነት ከፍተኛና በየጊዜው እያደገ የሚሄድ በጀት እየመደበ ይገኛል። መንግሥት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ እያካሄደ ያለውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ነክ መረጃዎች የማመንጨት ተግባርና ጥራት

እያጠናከረ ከመሆኑም በላይ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓቱን እንዲያስተባብርና ለልማት ዕቅዱ ጠቃሚ መረጃዎችን እንዲያቀርብና ለክትትልና ግምገማ ተግባሩም ማዕከል እንዲሆንና ብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓቱ የሚፈለገው ደረጃ ላይ እንዲደርስና እንዲሻሻል ከፍተኛ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡

የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓቱ መሻሻል ለዕቅድ ዝግጅት፣ ለክትትልና ለግምገማ ወይም ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን እንደገና ለማየት ብቻ ሳይሆን ለአጠቃላይ ህብረተሰቡ ለውሳኔ የሚረዱ መረጃዎችን በማመንጨትም ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ይህም ከብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥርዓቱ ለሁሉም ዜጋ ተደራሽ፣ አስተማማኝ የስታቲስቲክስ መረጃ ከማቅረብ በተጓዳኝ ለማኔጅመንት የመረጃ ሥርዓት የተሟላ ግብዓት በመሆን ለከፍተኛ የመንግሥት አካላትና ለእያንዳንዱ ዜጋም ተጠቃሚነቱን ከፍ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም ወጥ የሆነ ኦፊሺያል የስታቲስቲክስ ሥርዓት በመዘርጋት ያለውን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎችንና ለውጦች መደገፍ ብሎም ዓለማቀፋዊ ተነፃፃሪ በመሆን ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆንም መደረግ አለበት፡፡ የዚህ ዓይነት ሥርዓት ከተዘረጋ ደግሞ ፖሊሲዎችን፣ ፕሮግራሞችንና ስትራቴጂዎችን ከትክክለኛ መረጃ በመነሣት ተግባራዊነታቸውን ለመከታተል ያግዛል፡፡
በዚሁም መሠረት የኤጀንሲው ራዕይና ተልዕኮ በተገቢው መልኩ ለማሳካት እንዲቻል በአሁኑ ጊዜ ከ2002 - 2006 ያሉት ዓመታት የሚሸፍን አዲስ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ልማት ስትራቴጂ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ትግበራ የተገባ ሲሆን በአዲሱ ስትራቴጂ ዕቅድ አጠቃላይ የስታቲስቲክስ ሥርዓቱ አቅም የሚገነባበት፣ ሰነዱ ስትራቴጂውን ተግባራዊ ለማድረግ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን የፈተሸና የተለያዩ የስትራቴጂ ጭብጦችንና የሥራ ቅደም ተከተል ያለውና ከ2002 ዓ.ም. ጀምሮ በመተግበር ላይ የሚገኝ ነው፡፡

በተጨማሪም መንግሥት የቀጣዩን አምስት ዓመታት (2003 - 2007) የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ያዘጋጀ ሲሆን ከዚህ ጋር የተጣጣመ

አዲስ ብሔራዊ ስታቲስቲክስ ልማት ዕቅድና የአሠራር ስልት በመከለስና በማዘጋጀት የሥራ መርሃ-ግብርና የስታቲስቲክስ አቅም ግንባታ በአገር አቀፍ ደረጃ ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ ከዚህ ጋር በተያያዘ ከ2003 - 2007 ዓ.ም. የሚተገበርና ከንዋኔ ሂደት ላይ ያለውን የብሔራዊ የስታቲስቲክስ ልማት ስትራቴጂ መሠረት አድርጎ የተሻሻለ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ልማት ዕቅድና መርሃ-ግብር ተዘጋጅቷል፡፡

በዚህ የስታቲስቲክስ የልማት ስትራቴጂና ዕቅድ በርካታ የለውጥና የማሻሻያ ሥራዎች የሚሠሩ ሲሆን በዋነኛነት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲን በአዋጅ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር የመተግበርና የማስተባበር ኃላፊነት እንዲሁም ሙያዊ ሥነ-ምግባር የተላበሰ ባለሙያ የማፍራት፣ የጥራት ደረጃና ምደባን ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል አቅም የሚፈጥር ነው፡፡

በስታቲስቲክስ ልማት ስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመን ውስጥ የቤተሰብ ሰርቬይና የኢኮኖሚ ጥናቶች አሠራር በከፍተኛ ደረጃ እንዲሻሻልና እንዲለወጥ ይሠራል፣ እንዲሁም ሰፊና አጠቃላይ የሆነ የአዳዲስ ቴክኖሎጂን ለመጠቀም የሚያስችል የስታቲስቲክስ ልማት ስትራቴጂ በመሆኑ የሚካሄዱ ጥናቶች፣ ቆጠራዎች እንዲሁም ከአስተዳደራዊ መዛግብት የሚገኙ መረጃዎች ጥራትና ወቅታዊነት በዕቅድ ዘመኑ ከፍተኛ መሻሻል ይደረግባቸዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ቁልፍ ተግባራት ወደ ተጨባጭነት ለመለወጥ የሚያስችል የውጤት ተኮር ሥርት /BSC/ ሰነድ ተዘጋጅቶ ወደ ትግበራ የተገባ ሲሆን እንዲሁም የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ የለውጥና የማሻሻያ ሥራዎችን ይበልጥ ለማጠናከርና ተጨባጭ ለማድረግ የኤጀንሲውን ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች እንዲሁም የትኩረት መስኮችን በመቀመር በተቋም ደረጃ ከቡድንና ከግለሰብ ፈጻሚ የሚጠበቁ ውጤቶችን ለመለካት፣ ለመገምገምና ለመከታተል የሚያስችል በውጤት

ተኮር ሥርዓት ላይ የተመሠረተ የአምስት ዓመት የስታቲስቲክስ ልማት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ተዘጋጅቷል።

በዚሁ መሠረት የአምስት ዓመቱ የኤጀንሲው የስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች ተለይተው ስትራቴጂያዊ ግቦች ተቀምጠዋል፣

አገሪቱ የምትገኝበት የለውጥና የልማት ሂደትና መረጃ ስላለው ጠቀሜታ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የልማት አጀንዳ ድህነትና ኋላቀርነትን ማስወገድ ነው። ሁሉም የአገራችን የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ይህንኑ ድህነት የማስወገድ አጀንዳ በማሳካት ላይ ያተኩሩ ሲሆን ተጨባጭ ውጤቶችንም እያገኙ ናቸው።

ባለፉት ዓመታት በተካሄዱ የልማት ሥራዎች የተመዘገቡ ውጤቶችን፣ መልካም ተሞክሮዎችንና የሀገሪቱን ራዕይ መሠረት በማድረግ ህዝቡ በየደረጃው በሰፊት የተሳተፈበት የአምስት ዓመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተዘጋጅቷል። ዕቅዱ ሀገራችን ከ2003 - 2007 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የምትመራበት የዕቅድ ሰነድ እንዲሆንም ሚኒስትሮች ምክር ቤትና በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀድቋል።

የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን ዓላማ ለማሳካት የዜጐች የባለሙያዎች፣ የባለሀብቶችና የአመራሮች መሠረታዊ ያስተሳሰብ ለውጥ ይጠበቃል። ከዚህ አኳያ ለለውጥ፣ ለዕድገትና ለልማት እንቅፋት የሆኑ አስተሳሰቦችንና የጥገኝነት አመለካከቶችን በማስወገድ በተግባር ሊረጋገጡ የሚችሉ ልማታዊ አስተሳሰቦች ሽግግር ማድረግ ወሳኝ ጉዳይ ይሆናል።

በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት እንዲሳኩ የሚፈለጉ የዕቅዱ ዓላማዎችም ባለፉት ዓመታት ከተመዘገቡት ውጤቶችና እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ከ2012 - 2015 ባሉት ዓመታት ሀገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ከማሰለፍ ራዕይ ጋር ተሳስረው የሚታዩ ናቸው፡፡

### የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓላማዎች

የአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የሚከተሉት መሠረታዊ ዓላማዎች አሉት፡፡

1. አጠቃላይ ኢኮኖሚው በየዓመቱ ቢያንስ በአማካይ 11.2 በመቶ ዕድገትን በማስመዝገብ በኢኮኖሚያችን መታየት የጀመሩትን ማነቆዎች በማስወገድና በማቃለል የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ማሳካት፣
2. የትምህርትና ጤና አገልግሎት ሽፋንን መጨመርና ጥራቱን በማረጋገጥ ላይ የተመሠረተ ማህበራዊ ልማት በማካሄድ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ማሳካት፣
3. የተረጋጋ፣ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ መንግስትን በመፍጠርና በማጠናከር ለቀጣይ አገር ግንባታ ሥራ ምቹ መደላድል መፍጠር፣
4. ከላይ የተገለፁትን ዋና ዋና ዓላማዎች በተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ውስጥ በመፈፀም የልማቱን ቀጣይነት ማረጋገጥ ናቸው፡፡

### የዕቅዱ መሰረታዊ አቅጣጫዎች (Strategic Pillars)

የቀጣዩ አምስት ዓመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ፈጣን፣ ቀጣይና ፍትሃዊ ዕድገት በማረጋገጥ ሂደት የኢኮኖሚ መዋቅራዊ

ለውጥ የሚመዘገብበት እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ ይህንኑ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ መሠረታዊ አቅጣጫዎች፡-

1. ፈጣን፣ ቀጣይና ፍትሀዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ፣
2. የግብርናው ዘርፍ ዋና የዕድገት ምንጭ ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ፣
3. የኢንዱስትሪው ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ ቁልፍ ሚና እንዲጫወት ማስቻል፣
4. መሠረተ ልማትን ማስፋፋትና ጥራትን ማረጋገጥ፣
5. የማኅበራዊ ልማትን ማፋጠንና ጥራትን ማረጋገጥ፣
6. አቅም ግንባታንና መልካም አስተዳደርን ማሳደግ፣
7. የሴቶችንና የወጣቶችን ብቃትና ተጠቃሚነት ማሳደግ ናቸው፡፡

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የተቋቋመበት ዓላማ በቆጠራ፣ በናሙና ጥናት፣ በማያቋርጥ ምዝገባና ከአስተዳደር መዛግብት የተሰበሰቡ የኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና የዲሞግራፊያዊ የስታቲስቲክስ መረጃዎችን በተቀናጀ አሰራር ሰብስቦ፣ አቀነባብሮና ተንትኖ ለተጠቃሚዎች ማቅረብ ዋነኛው ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የመንግሥት መ/ቤቶችና ሌሎች አካላት የስታቲስቲክስ መዝገብ እያያዝ፣ የማያቋርጥ ምዝገባ አሠራርና የሪፖርት ሥርጭት እንዲዘረጉ የቴክኒክ ምክርና ድጋፍ የማድረግ፣ እንዲሁም ስለማያቋርጥ ምዝገባ፣ የአስተዳደራዊ መዛግብት መረጃ ከምችቶችና የአያያዝ ሥርዓት የማደራጀት አቅም የመገንባት ተግባራትን ማከናወንን ያጠቃልላል፡፡

በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት (2003 -2007) በኤጀንሲው በኩል ለሀገሪቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድና ለሚሊኒየሙ የልማት

ግቦች ክትትልና ግምገም የሚረዱ ጥናቶች በማካሄድ ላይ ይገኛል። (ምንጭ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ 2003-2007 ገጽ 157)

ይህ የሚያመለክተው በአገሪቱ ውስጥ እየተቀጣጠለ ላለው የዕድገት ማዕበል ጥራትና ወቅታዊ በሆነ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ወሳኝ ሚና እንዳላቸው ነው። በመሆኑም በእያንዳንዱ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት እንቅስቃሴ ውስጥ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳል ማለት ነው። አጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት የአገሪቷን የዕድገት ዕቅድና የመ/ቤቱን ራዕይ እውን በማድረግ ውስጥ የሕብረተሰቡ ድርሻ የላቀ ይሆናል። ምክንያቱም እያንዳንዱ ኤጀንሲው የሚሰበስበው የኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ መረጃዎች በሙሉ የሚገኙት ከሕብረተሰቡ ዘንድ በመሆኑ ነው።

ስለሆነም ሕብረተሰቡ ትክክለኛ መረጃን መስጠት መብትም ግዴታም ያለው መሆኑን በመገንዘብ ኃላፊነቱን መወጣት ይኖርበታል። ኤጀንሲው የአገሪቱ የስታቲስቲክስ ማዕከል ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች አሉት፡-

19. የስታቲስቲክስ መረጃዎችን በቆጠራ፣ በናሙና ጥናቶች፣ በማያቋርጥ ምዝገባና ከአስተዳደር መዛግብት ይሰበስባል፣ እንዲሰበሰቡም ያደርጋል፣ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ያደራጃል፣ ያቀነባብራል፣ ይተነትናል፣ በጽሑፍ ያወጣል፣ ያሰራጫል፣

20. በየወቅቱ የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የስታቲስቲክስ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ የበጀት ረቂቅ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣ ሌሎች የመንግሥት መ/ቤቶችና ተቋማትም በሥራ ላይ ማዋላቸውን ያረጋግጣል፣

21. ከመንግሥታዊ መ/ቤቶች ወይም ተቋማት ወይም የግል ድርጅቶች በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት የስታቲስቲክስን ሥራ በተመለከተ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣

22. የስታቲስቲክስ አሠራር ዘዴዎችን በተመለከተ የጥናትና ምርምር ተግባር ያከናውናል፣ የተገኙ ውጤቶችንም በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣

23. በመንግሥት መ/ቤቶችና ተቋማት፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና በግሉ ዘርፍ ውስጥ በስታቲስቲክስ ሥራ ለተሰማሩ ሠራተኞች መሠረታዊ አጫጭር የስታቲስቲክስ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ይሰጣል፣

24. አገራዊ የስታቲስቲክስ ሥራን ለማሻሻልና የሥራ መደራረብን ለማስወገድ የሥራ አፈጻጸም ፕሮግራሞችና መመሪያዎችን ያወጣል፣ በሥራ ላይ መዋላቸውንም ያረጋግጣል፣

25. የሚሰበሰቡትን መረጃዎች በተመለከተ ሥርዓት ይወስናል፣ ትርጉምና ምደባ ያወጣል፣ የሚሰበሰበውን መረጃ ዓይነትና ዝርዝር እንደዚሁም የሚሰበሰቡበትን ጊዜ ይወስናል፣ በዚሁ መሠረት እንዲፈፀም ያደርጋል፣

26. ዓለም አቀፍ ስታቲስቲካዊ ደረጃን ለመጠበቅ በአገሪቱ የሚሰበሰቡ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ከሌሎች አገሮች፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጋር ተነጻጻሪ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

27. በሀገራዊ የቆጠራና ናሙና ጥናት አማካይነት የሚሰበሰቡ ኢኮኖሚያዊ፣ የማህበራዊና የዲሞግራፊያዊ መረጃዎች የክልል መንግሥታትን ፍላጎት የሚያሟሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

28. የክልል መንግሥታት ጥያቄ ሲያቀርቡ አስፈላጊውን የስታቲስቲክስ መረጃ የመሰብሰብ፣ የማደራጀት፣ የመተንተንና በጽሑፍ የማውጣትና የማሠራጨት ዝግጅትን በመምራትና በማስተባበር ረገድ ይረዳል፤ እንደዚሁም የስታቲስቲክስ መዝገብ አያያዝ ሥርዓት መቋቋሙን ያረጋግጣል፤

29. የስታቲስቲክስ ተግባራትን ለማከናወን ከለጋሽ አገሮችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የገንዘብ፣ የማቴሪያልና የቴክኒክ ዕርዳታ የሚገኝበትን ሁኔታ በማመቻቸት በሚኒስትሩ እንዲፀድቅለት ያቀርባል፤

30. ከተያዘው ዕቅድና ፕሮግራም ውጪ ለሚቀርቡ የጥናት ጥያቄዎች ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ከመንግሥት መ/ቤቶችና ተቋማት እንዲሁም ከሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ለጥናቶቹ የሚያስፈልጉ የተወሰኑ ወጪዎችን እንዲሸፍኑ በማድረግና ቅደም ተከተል በማውጣት ጥናቶችን ያከናውናል፤

31. በሁሉም የስታቲስቲክስ ዘርፎች በስታቲስቲክስ ሙያ ሥልጠና ለሚሰጡ ማዕከላት ከውጪ ስለሚገኝ የሥልጠናና የቴክኒክ ዕርዳታ አጠቃቀም አስፈላጊውን ምክር ይሰጣል፤

32. የስታቲስቲክስ መዝገብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብን በሚመለከት የመንግሥት መ/ቤቶች ወይም ተቋማትና ሌሎች አካላት በተግባር

ሊያሟሉትና ሊከተሉት የሚገባውን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፣

33. በስታቲስቲክስና ተመሳሳይ ዘርፍ ከተቋቋሙ አገራዊ የሙያ ማህበራት ጋር ትብብር ይፈጥራል፣ እንደአስፈላጊነቱ ኮንፈረንሶች በሚካሄዱበት ጊዜ አስፈላጊውን ዕርዳታ ይሰጣል፣

34. ለሚያስራጫቸው የጥናትና የቆጠራ ውጤቶች እንዲሁም ጥሬ መረጃዎች ለመጠቀም የአገልግሎት ክፍያ ሊጠይቅ ይችላል፣

35. በስታቲስቲክስ ጉዳይ ሁሉ ለመንግሥት ምክር ይሰጣል፣

36. በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎችና አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፣ ስታቲስቲክስን የሚመለከቱ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።

## በ25ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች መሠረታዊ የኮሙኒኬሽንና የማስተዋወቂያ ስልቶች መነሻ

1. እያንዳንዱ ቅ/ጽ/ቤት ሥሙን በላሚራ በማጻፍ የዋና መ/ቤቱን ድረ ገጽ፣ ፖስታ ሳጥን ቁጥር፣ ሎጎ /በደብዳቤ መላላኪያ ወረቀታችን ላይ ይገኛል/ ሊታይ በሚችል ቦታ ላይ መትከል፣

2. እያንዳንዱ ቅ/ጽ/ቤት የፌዴራል መንግሥቱን ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ በደንቡ መሠረት በማዘጋጀት የመስቀልና የማውረድ ሥነ-ሥርዓትን ማከናወን፣
3. በቅ/ጽ/ቤቱ የተቋሙን ራዕይና ተልዕኮ ሠራተኞች ሊያነቡት በሚችሉበት ግልጽ ቦታ /በቢሮ ውስጥ፣ በማስታወቂያ ሠሌዳዎች ጽፎ በመለጠፍ ሠራተኞች ስለመ/ቤታቸው ያላቸውን ግንዛቤ ማሣደግ፣
4. ቅ/ጽ/ቤቱ ከሚገኝበት የከተማ አስተዳደር ጋር በመመካከር የተቋሙ ራዕይና ተልዕኮ የተፃፈበት የማስታወቂያ ሰሌዳ /ላሚራ/ የሚተከልበት አደባባይ

/ሥፍራ/ በመጠየቅ የአረንጓዴ አደባባይ /Green Square/ እንዲኖራቸው ማድረግ፣

5. ቅ/ጽ/ቤቱ ከሚገኝበት የከተማ አስተዳደር ጋር በመመካከር በከተማው ውስጥ በሚገኙ ቤተመፃሕፍቶች፣ የንባብ ቤቶች፣ ዩኒቨርስቲዎች የስታቲስቲክስ መረጃዎች እንዲደርሱ ከሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት ጋር መነጋገርና መረጃዎቹ በደረሱባቸው ተቋማት ለንባብ ዝግጁ መሆናቸውን መከታተል ፣ በቅ/ጽ/ቤቱ ውስጥ ከሁለት ቅጂ በላይ የሚገኙ ትርፍ የስታቲስቲክስ መረጃ ፓብሊኬሽኖች ካሉ ከላይ ለተጠቀሱት አካላት ለንባብ እንዲውሉ ማበርከት/መስጠት፣

6. ከዞን፣ ከወረዳ፣ ከቀበሌ ም/ቤቶች ጽ/ቤቶች ጋር በመመካከርና ኘሮግራም በማስያዝ በየደረጃው በሚደረጉ የሕዝባዊ ስብሰባዎች ላይ በመገኘት፣ እንዲሁም ከዩኒቨርስቲዎች፣ ኮሌጆችና ት/ቤቶች ጋር የቀረበ ግንኙነት በመፍጠር ልዩ ልዩ መድረኮችን ተጠቅሞ ስለ መ/ቤቱ ራዕይና ተልዕኮ ግንዛቤ ማስጨበጥና ለሥራችን ተባባሪ ማድረግ፣

7. ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ለአገር ልማት መፋጠን ያላቸውን አገራዊ ፋይዳ ለሕብረተሰቡ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ በዚህ መልክ እነዚህን ዋና ዋና ጉዳዮች መሠረት በማድረግ ከዋናው መ/ቤት ጀምሮ ሁሉም የመ/ቤቱ ሠራተኞች ለመ/ቤታችን የሥራ ሒደት ስኬት የበኩላቸውን ድርሻ በትጋት መወጣት እንዳለባቸው ይታመናል።።

## Survey and Capacity Building Programmes from 2010/11-2014

| Agriculture, Natural Resources & Environmental Statistics |
|---|
| • Crop Production Forecast Survey |
| • Crop Production Survey for Long and Short Rainy Season (Mehre & Belg Season) |
| • Farm Management Survey |
| • Land Utilization Survey |
| • Livestock, Poultry and Beehives Survey |
| • Utilization of Crop & Animal Production Survey |
| • Survey of Environmental Statistics |
| • Agricultural Census |
| • Natural Resource and Wildlife Survey |
| • Survey of Pastoral Areas |
| • Rural Economy Survey |

| Population Statistics |
|---|
| • Population Projection |
| • Ethiopian Demographic and Health Survey (EDHS) |
| • Inter-Censual Survey |
| • Compilation of Gender Statistics |
| • Project Proposal and Preparatory Activities for the 4th Population and Housing Census (the May 2017 Census) |
| • Compilation of Vital Statistics |

| Business Statistics |
|---|
| • Survey of Medium & Large Scale Manufacturing Industries |
| • Survey of Small Scale Manufacturing Industries |
| • Survey of Distributive Trade and Services |
| • Survey of Construction |
| • Maintain Business Register |
| • Compilation of Transport and Communication Statistics |
| • Compilation of Foreign Trade Statistics |
| • Construction of Producers' Prices and Quantity index for Manufactured Products |
| • Include ICT Module in Large Enterprise Survey |
| • Mining and Quarrying Statistics |
| • Business Expectation Surveys for Manufacturing |
| • Compilation of Distribution, Purifying and Distilling of Water |
| • Cottage and Informal Sector Survey |

| Household Surveys and Price statistics |
|---|
| • Survey of Producers' Prices of Agricultural Commodities |
| • Survey of Retail Prices of Goods and Services |
| • Survey of Agricultural Inputs |
| • Wages Index |
| • Consumer Prices Index (CPI) |
| • International Comparison Programme (ICP) |
| • Household Income, Consumption and Expenditure Survey |
| • Welfare Monitoring Survey |
| • Current Employment and Unemployment Survey |
| • Labor Force Survey |
| • Survey of Street Children |
| • Welfare Indicator Survey (including major HICE indicators) |
| • Time Budget Survey |

| Capacity Developments in the NSS |
| --- |
| • Network all CSA Regional Offices |
| • Improve Data Collection, Processing and Dissemination |
| • Establish Data Processing in CSA Regional Offices |
| • Develop Statistical Data Standards Document |
| • Developing Ethiopian Data Quality Assessment Framework and Conduct Sector Assessment |
| • Train Data Users and Producers |
| • Establish & Maintain Full Catalogue of NSS Official Statistics and Develop a Link to Other Websites |
| • Train Staff with MA and MSC Degree |
| • Construction of New Multi-Store Building /Statistical House/ and Furnishing |

| Household Surveys and Price statistics |
| --- |
| • Survey of Producers' Prices of Agricultural Commodities |
| • Survey of Retail Prices of Goods and Services |
| • Survey of Agricultural Inputs |
| • Wages Index |
| • Consumer Prices Index (CPI) |
| • International Comparison Programme (ICP) |
| • Household Income, Consumption and Expenditure Survey |
| • Welfare Monitoring Survey |
| • Current Employment and Unemployment Survey |
| • Labor Force Survey |
| • Survey of Street Children |
| • Welfare Indicator Survey (including major HICE indicators) |
| • Time Budget Survey |